# ታጠቅ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
የቴዎሪ መጽሔት

ታህሣሥ 1961 ዓ.ም.

# ታጠቅ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

የቲወሪ መጽሔት


አዘጋጅ፦ ነገደ ጐበዜ

የዝግጅት አማካሪ፦ ፍቅሬ መርድ



ታህሣሥ 1961 ዓ.ም. ዋጋው 1 ብር

ይዘት፡—  ገጽ


| | |
|---|---|
| ርዕሰ—አንቀጽ | 1 |
| የዓለም ተማሪዎች ትግል | 5 |
| የመደብ ቅራኔና የነገድ ቅራኔ በኢትዮጵያ | 20 |
| ከሕዝቡ ጋር ተሰለፍ!ከሱ ተማር!አብረኸው ታገል! | 29 |


---

ጠቃሚ አድራሻዎች፡—


በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
ፕሬዚዳንት፡— ግርማቸው ታደሰ
Karlsrogatan 15
Uppsala — SWEDEN

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
ፕሬዚዳንት፡— እንድርያስ እሸቴ
388 Orange St.
New Haven, Conn. 06511
U. S. A.

የትግላችን አዘጋጅ፡— እንዳርጋቸው አሰግድ
1 Berlin 19
Harbigstr. 1

የታጠቅ አዘጋጅ፡— ነገደ ጐበዜ
6183 Cité de Jazelles
Av. Jules Ferry
13 Aix-er- Provence
FRANCE


## ርዕሰ አንቀጽ

### «የማወቅ ዘመቻ»

እኛ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በሕዝባችን ላይ የተጫነውን የበደል ቀንበር ካየነውና ማጋለጥ ከጀመርን ብዙ ዓመታት አልፎናል።ለሕዝባችንም ችግሮች መፍትሄ የሚሆነው መሠረታዊ ለውጥ ብቻ መሆኑን በማመን ከሕዝቡ ጋር ባንድነት የሬቮሉሽናዊ ትግልን ጐዳና መርጠናል። ይህ አቋማችን «ባጋጣሚ» በአንዳንድ ወጣቶች ጉትጎችነትና በአንዳንድ ባለሥልጣኖች «ስህተትና ቸልተኝነት» እየተበረታታ እዚህ የደረሰ ሳይሆን የጊዜው ጭቆና ቀጥታና አስፈላጊ ውጤት ነው።የፊውዳሉ አቋም ፈርሶ ነፃ ኢትዮጵያ እስተምትመሠረትበት ጊዜ ድረስ፣ንቅናቄያችን እያደገ እንደሚሄድና በሃገራችን የነፃነት ትግል ውስጥ የግንባር ቀደምነት ቦታውን እንደሚይዝ ማንም ጥርጣሬ አይግባው።ወደድንም ጠላንም ይህ የታሪክ እርምጃ ውጤት ነው።ማንም ሊቋቋመው አይችልም።

«ዕድሜ ለመንግሥታችን» ከምንልበት ጊዜ ተነስተን ዛሬ «ዕድሜ ለኢትዮጵያ ሕዝብ» እስከልንበት ጊዜ ድረስ የተጓዝነው በጣም ረጅም መንገድ ነው።እንግዲህ ቆም ብለን የመጣንበትን መመልከትና ከሁሉም በላይ ደግሞ የምንጓዝበትን መንገድ ማሰላሰል ያስፈልጋል።

የፊውዳሉን አቋም በውሳኔዎችና በስሜት ብቻ መኰነንና «ግፍ ነው» እያሉ ማማረር አልፈነው የሄድነው ደረጃ ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት የሚገኘው በመሠረታዊ ለውጥ ብቻ ነው ብለን ካመን ከትውልዳችንና ከተበዝባዡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና ብዙ መራራ ትግልና መስዋዕትነት መጠየቁን መገንዘብ አለብን።እንግዲህ ድካማችንና መስዋዕትነታችን በከንቱ እንዳይሆን ካሁኑ ልንወስዳቸው የሚገቡን ብዙ እርምጃዎች አሉ።ከነዚህም አሁን በደረስንበት ታሪካዊ ደረጃ ታላቅ ቀዳሚነት ሊሰጠው የሚገባው ይህ «የማወቅ ዘመቻ»ያልነው ትግል ነው።ማንን ለማወቅ?—ዓለምን፣አፍሪካን፣ኢትዮጵያን።

ጅት በኩል ከባድ የሆነ አደራ ይጥልብናል ። ለተጨቋኙ የኢትዮጵያ
ሕዝብ አንድነት ለመሥራት፤በግንባር ቀደምነት ይህን የአንድነት ጉዳና
መትለምና ማሳየት ያስፈልጋል።በጠቅላላው እያንዳንዱ ወጣት ኢትዮ
ጵያዊ ዛሬ ሕዝባችንንም ሆነ ዓለምን የሚመለከቱትን ችግሮች ከሌሎ
ች አጥልቆ በመመርመር፤ከሌሎች አስቀድሞ በማቅረብና ከሌሎች አስ
ቀድሞ ትክክለኛውን ዴሞክራሲያዊ መፍትሄ በማሳየት ግንባር ቀደም
ትነቱን ማስመስከር ይኖርበታል። ለዚህ ሁሉ እንግዲህ ስለ አገራችን
ጠቅላላ ጊዜያዊ ሁኔታ፤ስለሕዝቦቿ ታሪክና የኑሮ ዘዴያቸው፤ስለዓለም
ሕዝብ ትግል ያለንን ጠቅላላ ዕውቀት በይበልጥ ማደርጀት ያስፈልገና
ል።አሁን ባለንበት ታሪካዊ ወቅት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት
ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባው ይህ«የማወቅ ዘመቻ»ያልነው መሆን አ
ለበት የምንለው ስለዚህ ነው።በአሜሪካ የሚገኙት ወንድሞቻችን ይህ
ን ትክክለኛ እርምጃ መውሰድ ጀምረዋል፤የምንደሰትበት ነው።በአው
ሮፓም የጥናት ክበቦች በያለበት ተቋቁመዋል።ከእንግዲህ ወዲያ ዓ
መታዊ ጉባዔዎችም ዋና ተግባራቸው ውሳኔ ማሳለፍ ብቻ ሳይሆን ሰ
ፋፊ ጥናቶች ማቅረቢያና መለዋወጫ ሆነው፤የጥናት ጉባዔ መልክ መ
ያዝ አለባቸው።በየቦታው የሚደረጉትን ጥናቶች እያቀናበረና እያባዛ
የአንዱ ድካም ያፈራቸውን ዕውቀቶች ለሁሉም ማዳረስና በጠቅላላ
ው የወጣቶችን የፖለቲካ ንቃት ከፍ ማድረግ በተለይ የዓለም አቀፍ
ማኅበራችን ተግባር ሊሆን ይገባል።

እንግዲህ ይህ እንዲከናወን ከያንዳንዳችን መጠነኛ ድካ
ምን፤ሥራ ወዳድነትን፤መተባበርንና ዲሲፕሊንን ይጠይቃል።በሙሉ
ልባችን የመረጥነው የመሰረታዊ ለውጥ ጉዳና አለን።ለሚያስከትለው
መራራ ትግልና መስዋዕትነት የተሰናዳን ከሆንን ለረጅሙ ጉዟችን ብ
ርታትና ብርሃን ለሚሰጠን ለዚህ ለ«ማወቅ ዘመቻ»ከጊዜአችን ከፍለ
የማንወስንለት ምክንያት በፍጹም አይታየንም።

«ታጠቅ»



## የዓለም ተማሪዎች ትግል

ከበላይ ተሰማ

ባለፈው ግንቦት ወር በፈረንሣይ አገር የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎ
ች ለመብታቸው በመታገል ጊዜ ያለፈበትን የቡርዡዋ የትምህርት አ
ሰጣጥና ግብ በመቃወም በያለበት ዩኒቨርሲቲውን ያዙት። መንግሥቱ
የጭቆና ኃይሎቹን ልኮ ከዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ አስወጣቸው። ትግ
ሉ ከዩኒቨርሲቲው መንገድ ላይ ወጣ።በግንቦት አሥር (እ·ኤ·አ) ሌሊ
ት ተማሪዎቹ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳደረጉ መንግሥቱ በብዙ ሺህ የሚ
ቆጠሩ ፖሊሶችን አሰልፎ ላከባቸው።ተማሪዎቹ ለራሳቸው መከላከያ
ከ፶፷ በላይ የሚሆኑ ምሽጎች ሠሩ፤ከፖሊሶቹ ጋር በታላቅ ቆራጥነት
ተዋጉ፤ስድስት መቶ ሰው ቆሰለ።በማግስቱ ፈጽሞ ከሁለተኛው የዓለ
ም ጦርነት ወዲህ በፓሪስ ከተማ ታይቶ የማይታወቅ የውጊያ ምልክ
ት — የተገለባበጡና የተቃጠሉ መኪናዎች፤የተቆፈሩ መንገዶች፤የድ
ንጋይ ቁልሎች፤የመስተዋት፤የንጨት፤የብረት ስብርባሪዎች — በየመን
ገዱ ታይተው ነበር።ከዚህም ጀምሮ ባሥር ቀን ውስጥ አሥር ሚሊዮ
ን ሠራተኞች የመሥሪያ ፋብሪካውንና ዕቃውን ይዘው — ከካፒታሊ
ስቶቹ ማርከው ማለት ይሻላል — ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ፤ሥራ አ
ቆሙ፤አንዳንዶቹን ካፒታሊስቶች በዚያው በሥራ ቦታ ቀፈደዷቸው።
የሞኖፖል ካፒታሊስቶች አገዛዝ ከፍጻሜ እንዲደርስና ሶሻሊዝም እ
ንዲመሠረት፤የሠራተኛው መደብ ሥልጣኑን እንዲይዝ የነበራቸውን
ታላቅ ፍላጐት በይፋ፤ባንደበትና በተግባር ገለጡ።ባጭር ጊዜ ውስጥ
በዳበረው ኢምፔሪያሊስት አገር፤በፈረንሣይ፤ግልጽ የሆነ ሬቦሉሽናዊ
ሁናቴ ተፈጠረ፤ቡርዡዋዚው ተርበተበተ።ነገር ግን የተማሪውንና የ
ሠራተኛውን ተጋድሎ አጣምሮ የሚመራ ሬቮሉሽናዊ ፓርቲ ስላልነበ
ረ ተስፋ ሊጣልበት ይቻል የነበረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ባጭሩ ተቀጨ

በፈረንሣይ የሬቮሉሽንን እሳት ጭሮ የነበረው የተማሪዎች
ተጋድሎ በዓለም ውስጥ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም የተማሪዎ
ች ትግል እንዳይደለ ማንም ያውቀዋል።በኢምፔሪያሊስት አገሮች፤በ
ሶሺያሊስት አገሮች፤በእስያ፤በአፍሪካና በደቡብ አሜሪካ ካለፉት ጥቂ

ስከ ዘጠና በመቶ የሚሆነው ሠርቶ-አደሩ ሕዝብ በፕሮዳክሺን እየተ
ሳተፈ የሞኖፖሎቹን ትርፍ ያዳብራል። ኢምፔሪያሊስቶች ሠራተኛው
ን ሕዝብና ተበዝባዥ አገሮችን እየዘረፉ በሚያገኙት ሀብት መልሰው
የብዝበዛ ዘዴያቸውን ያሻሽሉበታል፤የሕዝብ ፀርናየዓለም ሰላም ጠንቅ
የሆኑትን የመጨቆኛ ኃይሎቻቸውን ያስፋፉበታል፤ከዘረፋው ትርፍራ
ፊውን ደግሞ ለሠራተኛው ሕዝብ «የኑሮ ደረጃ ማሻሻያ» ያውሉ
ታል።

በኢምፔሪያሊስት አገሮች ሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ካልቸርና
ጥበብ ሁሉ የሚውለው ለቡርዡዋዚው አገልግሎት ነው። የፍትሕ፣የት
ምህርት፣የባሕል፣የሥነጥበብ፣የመገናኛ (ራድዮ፣ጋዜጣ፣ቴሌቪዥን)፤የ
ሃይማኖትና ሌሎችም ሕብረተሰባዊ ድርጅቶች በቡርዡዋዚው እጅ ና
ቸው። በሰው ልጆች መካከል የነበረውን ሰብዓዊ ግንኙነት ሁሉ በማጥ
ፋትና በርሱ ቦታ የገንዘብ ግንኙነት ብቻ በመተካት ቡርዡዋዚው በም
ዕራብ ኢሰብዓዊ የሆነ ሕብረተሰብን ከመፍጠር ደርሷል።

እርግጥ በኢምፔሪያሊስት አገሮች በረሃብና በቸነፈር የሚ
ሞተው ሕዝብ እጅግ በጣም ጥቂት ነው።እንዲያውም አብዛኛው ሠራ
ተኛ ራዲዮና ቴሌቪዥን፣መኪናና ፍሪጅደር፤ሌሎችም የኑሮ ማቃለያ
መሣሪያዎች አሉት።ነገር ግን እነዚህ መሣሪያዎች ዙረው እሰረኛ አድ
ርገውታል።ሠራተኛው በገዛ እጁ ሠርቶ ያፈራቸው ዕቃዎች ተመልሰ
ው የዕቃ ባሪያ ስላደረጉት ሰብአዊነቱ ተዳፍኖአል።ቡርዡዋዚው በመገ
ናኛ መሣሪያዎች ሁሉ በመጠቀም ሕይወትን የንዋይና የሥጋ ፍትወት
ጉዳይ ብቻ አድርጐ ስለሚያቀርብለት ሠራተኛው ወደቁም ሬሳ ተለው
ጧል።የሕይወቱ አዛዥ፤የወደፊት ዕድሉ ቀያሽ፤የሕብረተሰብ ወጣኝ ሕ
ዝቡ ራሱ አይደለም፤ነፃነትና ዴሞክራሲ ይባላል እንጂ ነፃነቱም ዴሞክ
ራሲውም የቡርዡዋዚው በመሆኑ በምዕራብ ያለው የሠራተኛ መደብ
የሀያኛው ክፍለ-ዘመን አዲስ ባሪያ ነው።

ነገር ግን ቡርዡዋዚው ውሸቱን ሁሉ እንደ ዕውነት አቅር
ቦ ሊዘልቅ አይችልም፤ሊሸሽጋቸው የማይችል ቅራኔዎች አሉ።እነዚህ
ን ቅራኔዎች ተማሪዎቹ በቅርብ ያውቋቸዋል።ለምሳሌ ከሕዝብ ውስጥ
ሠራተኛውና ገበሬው አንድነት እስከ ሰባ በመቶ ሲደርስ በዩኒቨርሲቲ



(3) እግረ መንገዳችንን የኢ.ት.ን.ነ.መ. የተባበሩት መንግሥታትን
«የሰው ልጅ መብት ቀን» ምክንያት በማድረግ ያስተላለፈው መልእክ
ት እንዲህ ይላል፦(ጽሁፉን ያገኘነው በንግሊዝኛ ነው።)

The fundamental ideas forming the basis of the Declaration of Human Rights stem from the recognition of the self-evident truth that the human person, created in the image of God, is invested with human dignity, inalienable, inviolable... The growing recognition of the fact that all men are members of one single human family, at the same time, imposes on us the realisation that this fundamental unity of mankind can grow and prosper only if it is based on freedom, liberty, universal justice and peace. The human rights and fundamental freedoms we have mentioned constitute the cornerstones of the constitution of the Ethiopian Empire.

የማር ወለላ በሆኑ በነዚህ ቃላትና በኤርትራ፣በባሌ፣በቦረና፣በሲዳ
ሞ፣በጐጃምና በሌሎችም ግዛቶች በሰላማዊው ሕዝብ ላይ በሚፈጸመ
ው ወንጀል መካከል ያለውን ቅራኔ አንባቢ ያስተውል!!

(4) "La révolution c'est le remaniement général de la société."

## የመደብ ቅራኔና የነገድ ቅራኔ በኢትዮጵያ

ከአውሳ እሳቱ

ከአድሃሪው የኢትዮጵያ አገዛዝ ባለሙያዎች ብዙ ጊዜ የሚሰማ አንድ አነጋገር አለ።ይኸውም «ኢትዮጵያ በብዙ ነገዶች የተከፋፈለች አገር ናት፣እያንዳንዱ ነገድ ለማፈንገጥ ይሞክራል።ዛሬ አንድነቱን ያገኘው በዙፋኑ ነው እንጅ ዙፋኑ ከጠፋ—እንዲያውም ኃይለ ሥላሴ ከሌለ—አገሪቱ ትበጠበጣለች።እያንዳንዱ አውራጃ ግዛቱን ይሸፍትበታል ...»የሚለው ነው።አባባሉ ይለወጥ እንጅ እንዲህ ዓይነቱን ወይም መሰሉን አስተያየት ሁላችንም ሰምተንዋል ወይም አስበንዋል።ዛሬ የአድሃሪዎች ዋና መሣሪያቸውና ማስፈራሪያቸው የሆነው፣ይህ በታሪክና በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ የተመረከዘ የሚመስል ሃሳብ ምን እንደሚያዝል ለማሳየት በዚች አነስተኛ ጥናት እንሞክራለን።ይህ የተባለው የኢትዮጵያ ነገዶች የርስ በርስ ግጭት የሚመነጨው ከምን እንደሆነና የሚፋፋመው ለምን እንደሆን፣በተለይ ከመደብ ቅራኔ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማስተዋል እንሞክራለን።

አንዳንድ ጸሐፊዎች በኢትዮጵያ እስከ ሰባ ነገዶች ይገኛሉ ይላሉ።ይህን ያህል ለማጋነን የነገድን ትርጉም በጣም ማጥበብ ያስፈልጋል።ለጥናታችን ነገድ የሚባለውን ቃል ሳናጠበው ለወትሮው አብዛኛው ሰው በሚጠቀምበት ሰፋ ባለ የሕብረተሰብ ክፍያ እንጠቀምበታለን።በዚህ ዓይነት ነገዶች የምንላቸው የጋላ፣የአማራ፣የትግሬ፣የሲዳሞ፣የጉራጌ፣የሱማሌ፣ወዘተ ... ናቸው።እያንዳንዶቹ በውስጣቸው ትልልቅና ቷንሽ ጐሣዎች አሉባቸው።ለጥናታችን መተንተኑ አይጠቅመንም።በቋንቋ፣በኃይማኖት፣በባሕላቸው፣በአኗኗራቸው እነዚህ ነገዶች የተለያዩ ናቸው።እስከ ቅርብ ጊዜም ድረስ የውስጣቸው ጐሣዎች እርስ በርሳቸው፣ወይም ነገድ ለነገድ፣አውራጃ ላውራጃ የሚዋጉ፣አሁንም በአንዳንድ ቦታ በየጊዜው የሚጋጩ ናቸው።እንግዲህ የነገድ ቅራኔ መኖሩን ለማስረዳት ግልጽ ነውና ጊዜ አናጠፋም።አማራ ከትግሬ፣ጋላ ከአማራ፣ሱማሌ ከአዳል፣መጋጨቱ፣ጦርነት ማድረጉ ያለ፣የቆየ ነገር ነው።ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ይህ ግጭት ከምን እንደሚመነጭ ነው።



የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ እድገት ለማጥናት ይህች ጽሁፍ አትበቃም።ቢሆንም በጠቅላላው ስንመለከተው፣ሕብረተሰብ ባለፈባቸው ልዩ ልዩ የታሪክ ምዕራፎች ውስጥ – ጥንታዊው የጋርዮሽ ኑሮ ከፈረሰበት ዘመን እስከዛሬው የካፒታሊዝም መደርጀትና የሶሻሊዝም መወለድ ድረስ – ዓይነተኛ የሚያደርጉትን ልዩ ልዩ ቅራኔዎች አዝሎ እንደነበረ እናውቃለን።ዋነኛው ቅራኔ የመደብ መሆኑን ሳይንስ ያስተምረናል።በደሀና በሃብታም፣በባለርስትና ባራሽ፣በባሪያና በጌታ ያለው ይህ ቅራኔና የሚያስከትለው ትግል የታሪክ ሞተር ነው።ነገር ግን በኢትዮጵያና በመሰሏ አገሮች የሁለተኛ ደረጃ ቅራኔዎች ዋናውን ቅራኔ በመሸፈን የገነነ ቦታ ይዘው ይገኛሉ።ከእነኚህም ቅራኔዎች አሁን የምንመለከተው የነገድ ቅራኔ የተፈጠረው አገሪቱ በተስፋፋችበት ጊዜ ልዩ ልዩ ነገዶች ታሪካቸውን፣ባሕላቸውን፣የሕብረተሰባቸውን አቋም ይዘው ሲመጡ፣የአሸናፊ ነገድ ገዢዎች እነዚህን ተሸናፊ ነገዶች ከመጨቆን በላይ ዓይነተኛ የሚያደርጋቸውን ታሪካቸውን፣ባሕላቸውን፣ለማጥፋትና የራሳቸውን ባሕል ለማውረስ በመሞከራቸው ነው።እያንዳንዱ ነገድ በውስጡ የመደብ ቅራኔ አለበት።ከሌላ ነገድ ጋር በተጋጨበት ጊዜ ይህ የውስጥ ቅራኔ ለጊዜው ሊደክምና ከሌላ ነገድ ጋር ያለው ቅራኔ ሊያይል ይችላል።ለምሳሌ ግራኝና የምስራቅ ነገዶች ሰሜንንና ምዕራብ ኢትዮጵያን ሲወጉ የአማራና የትግሬ ሕዝብ ከገዢዎቹ፣ከጨቋኞቹ ነገሥታትና መሳፍንት ጋር ተሰልፎ የምስራቅን ወረራ ተከላከለ።ታሪኩን ሳንዘረዝር የዛሬውን ሁኔታ እያየን ያለውን የነገድ ቅራኔ ልክ ከአንደኛው ደረጃ ቅራኔ፣ከመደብ ቅራኔ፣ጋር እንመልከተው።

ስምንተኛው ጠቅላላ ጉባዔ የኢትዮጵያን ሕብረተሰባዊ መደቦች ሲዘረዝር በአምስት ይከፍላቸዋል።

1ኛ) ፊውዳላዊ መደብ
2ኛ) ቡርዡዋ መደብ
3ኛ) አነስተኛ (ፔቲ) ቡርዡዋ መደብ
4ኛ) የሠራተኛ መደብ
5ኛ) የገበሬ መደብ

የፊውዳሉን መደብ እንደገና በሁለት ይከፍለዋል።

ሀ) ንጉሣዊ ቤተ–ሰብ፣መሳፍንትና መኳንንት፣ታላላቅ ካህናትና ታላላቅ ባለርስት፣ታላላቅ ባላባት

«እንደ ድሪቶ የተጠጋገነ የሃሰት ተረትን መለኮታዊ መልክ በመስጠት፣ቤተ ክርስቲያን እየባረከች የምታቀርበውን የአገዛዝ ፍልስፍና ድጋፍ በማድረግ የፖለቲካን ሥልጣን በጃቸው ጨብጠዋል(1) በአሁኑ ጊዜ—ከኢትዮጵያ ታሪክ አመጣጥ የተነሳ—ከዚህ መደብ አባሎች አብዛኞቹ የመነጩት ከሸዋ አማራ ነገድ ነው።በኢትዮጵያ ንጉሣዊ ቤተ–ሰብ ዘንድ የተለመደው የጋብቻ መተሳሰር ንጉሣዊውን ቤተ–ሰብ የወሎ ጋላ ወይም የትግሬ ዘር እንዲኖርበት ቢያደርገውም ሥሩ፣ ምንጩ ያው የሸዋ አማራ መሆኑን አይለውጠውም።ከትግሬ፣ከጐጃም፣ከበጌምድር ... ወዘተ. የሚወለዱ ታላላቅ ባላባቶች ቢኖሩም ጊዜያዊ እድገታቸውንና ማዕርጋቸውን የሚያገኙት በሸዋው ቤተ መንግሥት መልካም ፈቃድ(!!) ነው።ይህ መደብ «በተቀሩት ሕብረተሰባዊ መደቦች ጭንቅላት ላይ በመቀመጥ መላውን ሕዝብ ጨቁኖ ይዞ በሚያንገፈግፍ አኳኋን የላብ–አደሩን የሥራ ፍሬ እንደመዠገር ይመጣል»(2)። መላው ሕዝብ ሲል ነገድን አይለይም።ምንም እንኳ የዚህ መደብ መሪ የሸዋ አማራ ቢሆን ዘረፋውንና ጭቆናውን የሚያደርገው አማራ፣ጋላ፣ትግሬ... ወዘተ. ሳይለይ በሁሉም ሕዝብ ላይ ነው።

ማንኛውም መደብ የራሱ አይዲዎሎጂ አለው።የዚህም መደብ አይዲዎሎጂ የታወቀ ነው።ከመለኮታዊው የሥልጣን ምንጭ ተረት ጋር የሚወሩ ሌሎች ተረቶች አሉ።«የኢትዮጵያ ሃይማኖት ክርስትና ነው፤የኢትዮጵያ ቋንቋ አማርኛ ነው»ይሉናል።ሌላው ሃይማኖት፣ሌላው ቋንቋ የባዕድ ነው ማለት ነውን ? ሃገር የጋራ ናት ሲሉ ማንኛውንም የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ማንኛውንም የኢትዮጵያ መሬት፣የኢትዮጵያን ሀብት መዝረፍ እንችላለን ማለታቸው ነው እንጂ ሃገሪቱ የሕዝቡ ናት ማለታቸው አይደለም።የጋራ የሚለው ቃል የነሱ ጋርዮሽ ነው እንጂ ሌላውን አይጠቀልልም።

ለ) በዚሁ በፊውዳል መደብ ውስጥ የሚቆጠሩ «ታናናሽ ባላባቶችና መጠነኛ ባለርስቶች» ናቸው።



1) ዛሬ በኢትዮጵያ የነገድ ብጥብጦች የሚባሉት ከመደብ ትግል ጋር የተሳሰሩና የማይነጠሉ መሆናቸውን፤
2) ኢትዮጵያን የሚገዛው፣ከፍተኛው ፊውዳላዊ መደብ ከአንድ ጐሣ የፈለቀ መሆኑን፤መሠረቱን ለማጠንከርና መልኩን ለመለወጥ ሲል የተጠቀመባቸው ልዩ ልዩ ዘዴዎች (ጋብቻ፣ሹመት፣ክርስትና ማንሳት ... ወዘተ.) ምንም ስላልጠቀሙት አማራ–ክርስቲያን ባልሆኑ አውራጃዎች ሁሉ የሚነሱ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች በነገድ ስሜት ላይ መመርኮዛቸውን፤
3) የዛሬው ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አንድ ግንባር እንዳይኖረው መከልከሉን፤የሚነሳው ሕዝባዊ ንቅናቄ ሁሉ የነገድን ስሜት በማዘሉ የአካባቢዎቹን ዝቅተኛ ፊውዳሎችና ከፍተኛ ቡርዡዋዎች ጭምር መሪነት እየሰጠ የተነሳበትን ግብ ሲስት አድሃሪውን መንግሥት የኢትዮጵያን አንድነት ጠባቂ አስመስሎ የመላውን ሕዝብ ጥቅም መጉዳቱን፤

ይህ የነገድ ቅራኔ ቀዳማዊ የሆነውን የመደብን ቅራኔ ዛሬ ገበሬውና ሠራተኛው እንዳይረዳው በማድረጉ ትግላችንን ወደኋላ ጐትቶታል።ነገ አዲሲቱን ኢትዮጵያ በምንፈጥርበትና በምንገነባበት ጊዜ ተከፋፍለን የአድሃሪው አገዛዝ የበላይ ጠባቂ፣የኢምፔሪያሊዝም፣እራት እንዳንሆን የዚህን ቅራኔ ትክክለኛ መፍትሄ ማግኘት አለብን።

ከፍተኛውን ፊውዳላዊ መደብ በማጥፋት፣ዝቅተኛውን ፊውዳላዊ መደብ «የነፍጠኛ» መልክ ከያዘበት ቦታ ሁሉ በመንቀል፣ባላባት የተባሉት አወላዋዮች ያላቸውን የበዝባዥነት ቦታ ለገበሬው በመግለጽ የዚህን ቅራኔ መስፋፊያ አቋሞች ማጥፋት ይቻላል።

አገር የጋራ የምትሆነው፡—

—የነፃነት ፈሊጦች ሁሉ በአንደበት ሳይሆን በተግባር ላይ ሲውሉ፤

—መሬት የአራሹ እንጂ የሌላ አየር ወለድ ኃይል አለመሆኑ ሲረጋገጥ፤

—የኢትዮጵያ ባሕሎች ሁሉ እኩል ሲጠበቁ
ነው።

የነገድ ቅራኔ የሚጠፋው፡—
—ሃገሪቱ ስትለማ፤
—አውራጃ ከአውራጃ፤መንደር ከመንደር፤ነገድ ከነገድ
ሲገናኝና ሲተሳሰር፤
—የነገድ ስሜቶች ጠፍተው አንድ ብሄራዊ ስሜት ሲ
ፈጠር
መሆኑን መገንዘብ አለብን።

ለዚህ ትልቅ ዓላማ ሊሠሩ የሚችሉ የነገድን ስሜት መንጥ
ቀው የወረወሩ፤ከሁኑ አማራ፤ጋላ፤ኤርትሪያዊ ... ወዘተ. ነን ብለው የ
ማያስቡ፤የቋንቋና የሃይማኖት እስረኞች ያልሆኑ፤የጐሣቸውን፤የነገዳቸ
ውን፤የኢትዮጵያንም ድንበር አልፈው የሚያስቡ ናቸው።

---

ማብራሪያዎች፡—

1) የዛግሬብን ስምንተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች ገጽ 7 ተመልከት።
2) የዛግሬብ ውሳኔዎች ገጽ 8
3) የዛግሬብ ውሳኔዎች ገጽ 10



ትን ለማቆም ተነሳ።በባሌ ያለው የመደብ ሁኔታ በሐረርጌም ስላለ ነው።
በእነዚህ ሁለት አገሮች የሚታየው፤የአገሩ ተወላጅ የሆኑት ባላባቶች
ከገበሬው ጋር ሆነው ነፍጠኞችን ለማስወጣት መሞከራቸውና ፊውዳ
ላዊ አገዛዙ ሁልጊዜ ከነፍጠኞች ጋር መሰለፉ ነው።በቅርብ የታየው የ
ቱለማና ሜጫ ማኅበር ጉዳይም ይህንኑ ይመስላል።ብዙ አስተዋይ ተመ
ልካቾች እንደሚሉት ይህ ማኅበር በሸዋና በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት ጋላ
ሕዝብ ዘንድ የማነቃቃት መንፈስ ስለፈጠረ፤በኤረርና በከረዩ አውራጃ
ግዛት(አዳማ፡ቢሾፍቱ)፤በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት ብዙ ተከታይ አግኝቶ ሕ
ዝባዊ ንቅናቄ ስለሆነ በተለይ የከፍተኛው ፊውዳላዊ መደብ አባሎችን
አሰጋቸው።(ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤የወንድማቸው የመኰንን ሀብተ ወል
ድ ወራሾችና ጥገኞች፤የአሩሲው ገዢ ሣህሌ ድፋዩ ከዱከም – አዳማ
እንዲሁም አሩሲ ውስጥ ሰፋፊ መሬቶች እንዳሏቸው የታወቀነው።)

የሸዋንና የአሩሲን ባላባቶች ከተራው ገበሬ ጋር ያስተሳሰራ
ቸው በመሬት ዘረፋው ላይ «አማራው» — ከፍተኛው ፊውዳላዊ መደ
ብ — ስለቀደማቸው፤ለዘረፋው እንዲመቸው የሚያደርገው የአማራን
ባሕል ማስፋፋት የነሱን ባሕልና ጥቅም ስለነካባቸው ነው።ዛሬ ቢሾፍቱ
ደብረ ዘይት፤አዳማ ናዝሬት — ምናልባት ነገ አሰላ ቴል አቢብ — ሲባ
ል፤ከባሕል ጭቆና ጋር የጥቅም ግጭት እየከረረ ሲሄድ የእነዚህን ባላ
ባቶች ከተነጠቀው ሕዝብ ጋር መሰለፍ ይፈጥራል።የነዚህ ባላባቶች አ
ይዲዎሎጂ የሚያስተምረው «አማራ ጨቆነህ፤አማራ መሬትህን ቀማህ፤
ቋንቋህን ገደለው፤ሚስትህን ሳይቀማህ ተነሳ» ነው።ድሀው፤የተጨቆነ
ው የአማራ ገበሬ ከሚበዘብዙትና ከሚጨቁኑት ፊውዳሊስቶች ጋር አ
ብሮ ይወቀሳል።

አሁን ደግሞ በሰሜንና በሸዋ አማራ አገር መካከል ያለው
ን ሁኔታ እንመልከት።በነዚህ አገሮች ያሉት የዝቅተኛው ፊውዳላዊ መ
ደብ አባሎች የአገሩ ተወላጆች ስለሆኑ በነርሱና በገበሬው መካከል የ
ነገድ ቅራኔ የለም።ቅራኔው ያለው በዝቅተኛውና በከፍተኛው ፊውዳላ
ዊ መደቦች መካከል ነው።የዝቅተኛው ፊውዳላዊ መደብ አባሎች — ከ
ፍተኛው መደብ ስለሚጨቁናቸው — እነሱን የሚጠቅም መሠረታዊ
ለውጥ እንዲመጣ ይፈልጋሉ፤በበታቻቸው የሚገኘውን የጪሰኛ ገበሬ

ኑሮ ሲመለከቱ ግን ለውጡ ርቆ በመሄድ የራሳቸውን ጭምር የሚያሳጣ
ቸው ስለሚመስላቸው እያጉረመረሙ መኖርን ይመርጣሉ።አንዳንዴ ግ
ን (በቅርቡ ጐጃም እንደታየው) የራሳቸውን ወገን ጥቅም በሙሉ ሲደ
ግፉ ይታያሉ ።

አድሃሪው መንግሥት ሥልጣኑን ለማረጋገጥና እድሜውን ለ
ማርዘም ሲል በዚህ በነገድ ቅራኔ ይጠቀማል ። ለአስተዳደሩ ታማኝ የሚ
ያገኘው በትውልዳቸው ወይም በአስተዳደጋቸው ከሚቀርቡት ሰዎች
መሆኑን በማወቅ ሹማምንቱን ከአማርኛ ተናጋሪዎችና ከክርስቲያኖች
መካከል ይመርጣል ። የኢትዮጵያን አንድነት የሚያምንበት ለማስመሰ
ል ሌሎችንም በመጠኑ ይቀላቅላል ። በተለይ ወታደር ሲቀጥር ክርስቲያ
ኖችና አማሮችን ለመምረጥ ይሞክራል ፤ ፓሊሱ እንኳ ሳይቀር የየመን
ደሩ ተወላጅ እንዳይሆን ይጥራል ። በውጭ ፓለቲካው የፈጠረውን የእ
ስልምና ፍርሃት በጦር ሠራዊቱ ውስጥ አሳድሮ የመከላከያውን ጦር ሕ
ዝብ የመጨፍጨፊያ መሣሪያ አድርጎታል።ዛሬ የሚሰበከውን «ኢትዮ
ጵያ የክርስቲያን ደሴት በመሆኗ ዙሪያዋ ያሉት እስላም አገሮች ሊያጠ
ፏት ይፈልጋሉ፤የኢትዮጵያም እስላሞች የነሱ ተባባሪዎች ናቸው » የ
ሚለውን ተከትለው የቢሮክራሲው የጦር ሠራዊት አባሎች ኤርትራ፤
ባሌ፤ኦጋዴን ሲዘምቱ ለአገራቸው የሠሩ ይመስላቸዋል ።

ነገር ግን ከዚህ በላይ እንዳስረዳነው እነዚህ ነገዶች የሚነሱ
ት በአማራ ላይ፤በክርስቲያን ላይ፤በኢትዮጵያ ላይ አይደለም፤ኢትዮጵ
ያን በሚገዛው፤በከፍተኛው ፊውዳላዊ መደብ ላይ ነው ። የነሱ ጦርነት የ
ነገድ ጦርነት የሚመስለው ይህ ገዥ መደብ ከአንድ ነገድ የፈለቀና የ
ሚመረከዘውም በዚሁ ነገድ በመሆኑ ነው ። ይህም ማለት ይህንን ነገድ
አንተ ነህ የምትገዛው፤ያንተ ነኝ እያለ ገበሬውንና ዝቅተኛውን ፊውዳ
ል መደብ ያታልለዋል ማለት ብቻ ነው ። እንግዲህ አድሃሪው መንግሥ
ትም ሆነ የሶማሊያ ራዲዮ ወይም የኤርትራ ነፃነት ግንባር የሚያወሩት
ተቃራኒ ፕሮፓጋንዳ ሃሰት መሆኑን ያሳየን ይመስለናል ።

ዝርዝራችንን አቁመን የጥናታችንን ውጤት ያየን እንደሆ
ነ የሚከተሉትን መደምደሚያዎች እናገኛለን ።



1) ዛሬ በኢትዮጵያ የነገድ ብጥብጦች የሚባሉት ከመደብ
ትግል ጋር የተሳሰሩና የማይነጠሉ መሆናቸውን፤
2) ኢትዮጵያን የሚገዛው፤ከፍተኛው ፊውዳላዊ መደብ ከ
አንድ ጐሣ የፈለቀ መሆኑን፤መሠረቱን ለማጠንከርና
መልኩን ለመለወጥ ሲል የተጠቀመባቸው ልዩ ልዩ ዘ
ዴዎች (ጋብቻ፤ሹመት፤ክርስትና ማንሳት ... ወዘተ.)
ምንም ስላልጠቀሙት አማራ—ክርስቲያን ባልሆኑ አው
ራጃዎች ሁሉ የሚነሱ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች በነገድ
ስሜት ላይ መመርከዛቸውን፤
3) የዛሬው ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አንድ ግንባር
እንዳይኖረው መከልከሉን፤የሚነሳው ሕዝባዊ ንቅናቄ
ሁሉ የነገድን ስሜት በማዘሉ የአካባቢዎቹን ዝቅተኛ ፊ
ውዳሎችና ከፍተኛ ቡርዡዋዎች ጭምር መሪነት እየሰ
ጠ የተነሳበትን ግብ ሲስት አድሃሪውን መንግሥት የኢ
ትዮጵያን አንድነት ጠባቂ አስመስሎ የመላውን ሕዝብ
ጥቅም መጉዳቱን፤

ይህ የነገድ ቅራኔ ቀዳማዊ የሆነውን የመደብን ቅራኔ ዛሬ ገ
በሬውና ሠራተኛው እንዳይረዳው በማድረጉ ትግላችንን ወደኋላ ጐት
ቶታል ።ነገ አዲሲቱን ኢትዮጵያ በምንፈጥርበትና በምንገነባበት ጊዜ
ተከፋፍለን የአድሃሪው አገዛዝ የበላይ ጠባቂ፤የኢምፔሪያሊዝም፤እራ
ት እንዳንሆን የዚህን ቅራኔ ትክክለኛ መፍትሄ ማግኘት አለብን ።

ከፍተኛውን ፊውዳላዊ መደብ በማጥፋት፤ዝቅተኛውን ፊው
ዳላዊ መደብ «የነፍጠኛ» መልክ ከያዘበት ቦታ ሁሉ በመንቀል፤ባላባት
የተባሉት አወላዋዮች ያላቸውን የበዝባዥነት ቦታ ለገበሬው በመግለ
ጽ የዚህን ቅራኔ መስፋፊያ አቋሞች ማጥፋት ይቻላል ።

አገር የጋራ የምትሆነው፦

—የነፃነት ፈሊጦች ሁሉ በአንደበት ሳይሆን በተግባር ላ
ይ ሲውሉ፤
—መሬት የአራሹ እንጂ የሌላ አየር ወለድ ኃይል አለመ
ሆኑ ሲረጋገጥ፤

—የኢትዮጵያ ባሕሎች ሁሉ እኩል ሲጠበቁ ነው።

የነገድ ቅራኔ የሚጠፋው፡—

—ሃገሪቱ ስትለማ፤

—አውራጃ ከአውራጃ፤መንደር ከመንደር፤ነገድ ከነገድ ሲገናኝና ሲተሳሰር፤

—የነገድ ስሜቶች ጠፍተው አንድ ብሄራዊ ስሜት ሲፈጠር

መሆኑን መገንዘብ አለብን።

ለዚህ ትልቅ ዓላማ ሊሠሩ የሚችሉ የነገድን ስሜት መንጥቀው የወረወሩ፤ከሁኑ አማራ፤ጋላ፤ኤርትሪያዊ ... ወዘተ. ነን ብለው የማያስቡ፤የቋንቋና የሃይማኖት እስረኞች ያልሆኑ፤የጐሣቸውን፤የነገዳቸውን፤የኢትዮጵያንም ድንበር አልፈው የሚያስቡ ናቸው።

---

ማብራሪያዎች፡—

1) የዛግሬብን ስምንተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች ገጽ 7 ተመልከት።

2) የዛግሬብ ውሳኔዎች ገጽ 8

3) የዛግሬብ ውሳኔዎች ገጽ 10



ዎች ውስጥ የሠራተኛና የገበሬ ልጆች በቁጥር አንድነት ከሃያ አምስት በመቶ በታች ናቸው(1)።እንደዚያም ሆኖ ተማሪዎቹ የሚሰለጥኑት ለቡርዡዋዚው የኅርዳክሽን መኪና እንዲውሉ ነው እንጂ ሕብረተሰብን በተሻለ ሰብዓዊ መንገድ እንዲያደራጁት ወይም ሕይወታቸውን ሰለፊው ሕዝብ አገልግሎት እንዲያበረክቱት አይደለም። ትምህርቱ በዘዴውም በግቡም አድሃሪ ሆኖ ይገኛል።ተማሪዎቹ ይህንን ይገነዘቡታል

ቡርዡዋዚው የጥፋት መሣሪያዎችን በብዛት እንደሚሠራና በፍጥረቱ የሰላም ጠር መሆኑን ሸሽጐ ሊያመልጥ አይችልም።ስለ ዓለም ሰላም በሚያወራው ወሬና በየዕለቱ «በሕግና በፀጥታ» አመካኝቶ በሚፈጽመው ወንጀል መካከል ትልቅ ቅራኔ አለና።ተማሪዎች ይህንንም ያውቁታል።እንግዲህ በብሔራዊ ደረጃ የሚታገሉት ይህንን አድሃሪና ኢሰብዓዊ የሕብረተሰብ አቋም መንቅሎ ለመጣልና ሕዝቡ በፈቃዱ የወደፊት ዕድሉን የሚቀይስበት፤የሕብረተሰብን ሰብዓዊና የተፈጥሮ ሀብት ለጥፋት ሳይሆን ለልማት የሚያውልበት፤እኩልነትና ነፃነት፤አእምሮ የነገሠበት፤ሕብረተሰብ ለመፍጠር እንዲቻል ነው።

ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ወደ ምስራቅ አውሮፓ አገሮች ስንዞርም ተማሪዎች በብሔራዊ ደረጃ የሚታገሉት ለነፃነት፤ለዴሞክራሲና ለሶሻሊዝም መሆኑን እናያለን።በምስራቅ አውሮፓ ሶሺያሊስት ሬቮሉሽን ከተደረገ በኋላ የሠራተኛው መደብ ሥልጣኑን ይዞ ነበር።ቢሆንም ከታሪክ አስተዳደግ የተነሳ ሥልጣኑን የያዘው የሠራተኛ መደብ ወዲያውኑ ቡርዡዋዚውን ከነሥረ-መሠረቱ መንቅሎ ሊያጠፋው አልቻለም።በተለይም በአይዲዮሎጂ፤በሥነጽሁፍ፤በሥነጥበብ፤በባሕልና በጠቅላላውም መንፈሳዊ አቋም (ሱፐርስትራክቸር) በኩል የሠራተኛው መደብ የማያወላውል ድልን በቡርዡዋዚው ላይ ለማግኘት አልቻለም ነበር።ከዚህና ከኢምፔሪያሊዝም መስፋፋት የተነሳ በምሥራቅ አውሮፓ የሠራተኛው መደብ መሪ የነበረው ፓርቲ ፍጥረቱን ለውጦ ወደተቃራኒው ተለወጠ።ከዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ወደ ቢሮክራታዊ ፀረ ነፃነት ፓርቲ፤ከግንባር ቀደምትነት ወደእርምጃ መሰናከል፤የሕዝብ ክፍል ከመሆን ከሕዝብ በላይ ወደመሆን፤ ተለወጠ።የስንቱን መቶ ሺህ ጀግኖች ደም አሳልፎ በመስዋዕትነት ለሬቮሉሽኑ በመስጠት

(1) ቁጥር ለተደረገባቸው ሁሉ ተጨማሪ ማብራሪያ በየዕሑፎቹ መጨረሻ ይሰጣል።

የተገኘው የሠራተኛው መደብ ጥቅምና ነፃነት እየዳበረ በመሄድ ፈን
ታ በቢሮክራታዊው ፓርቲ ጥቅም ተሸፍኖ ቀስ በቀስ እየመነመነ ሄደ
ዛሬ በምስራቅ አውሮፓ የሚታየው የሠራተኛው መደብ ሁኔታ በኢ
ምፔሪያሊስት አገሮች ያለውን ሁኔታ እየመሰለ በመሄድ ለነፃነትና ለ
እርምጃ፤ለአዲስ ዓይነት ሕብረተሰብ የሚደረገውን ጥረት የሚቃወም
ሆኗል፤ማለት፤ፀረ–ሬቮሉሽናዊ ወይም አድሃሪ ሆኗል።

ባንድ በኩል በሥልጣን ላይ ያሉ ቢሮክራቷዊ ፓርቲዎች
ለወጣቱ ትውልድ ለመስጠት የሞከሩት የተሳሳተ የሶሻሊዝም ሥዕል
ይህ ሆኖ ስለተገኘ፤በሌላ በኩል ደግሞ የኢምፔሪያሊስት ፕሮፓጋንዳ፤
ጋዜጣው፤በመጽሔቱ፤በሲኒማው፤ወደነዚህ አገሮች ገብቶ የወጣቱን መ
ንፈስ እንዲመርዝ በሩ በሰፊው ስለተከፈተለት፤ላጭር ጊዜ ወጣቱ ት
ውልድ ተታለለ።በሬቮሉሽናዊ ርዕዮተ–ዓለም ፈንታ የኢምፔሪያሊስ
ቶችን «ሥልጣኔ» እንደ መለኪያ ሚዛን ወስዶ በሥልጣን ላይ ያለው
ን ቢሮክራታዊ አቋም ተቃወመ።ነገር ግን ላጭር ጊዜ ብቻ ነው።የቼኮ
ዝሎቫኪያ ወረራ የብዙዎችን ዓይን ከፍቷል፤ዛሬ መከተል ያለባቸውን
መስመር በመፈለግ ላይ ያሉት የምሥራቅ አውሮፓ ተማሪዎች ቀድሞ
ውንም ቢሆን ለማስወገድ የጣሩት ውሰጣዊውን ብሔራዊ ቢሮክራቲ
ክ አቋም ነበር።

በኢምፔሪያሊስት አገሮችና በምሥራቅ አውሮፓ ያሉት
ተማሪዎች ትግል ከዚህ በላይ ተጠቅሶአል።በተበዝባጋ አገሮችስ ተ
ማሪዎች በብሔራዊ ደረጃ የሚያደርጉት ትግል ምን ዓይነት ነው?

በተበዝባጋ አገሮች የሕብረተሰብን አቋም ዓይነተኛ የሚ
ያደርገው በሰው ልጆች መካከል ያለው የሃብት ልዩነትና ከርሱም የሚ
ፈልቀው የመብት ልዩነት ነው።በብዙዎች የእስያ፤ያፍሪካና የደቡብ አ
ሜካሪ አገሮች ከአውሮፓ የዛሬ ሦስት መቶ ዓመት የጠፋው ፊውዳላ
ዊ አቋም፤ከኢምፔሪያሊዝም መስፋፋት የተነሳ እንደያገሩ መልኩን
ለውጦ ውጥንቅጥ ይሁን እንጂ፤አሁንም አለ።የሕብረተሰቡ የመጀመ
ሪያና ዋና የፕሮዳክሽን መሣሪያ የሆነውን መሬትን የያዙት እፍኝ የማ
ይሞሉ ታላላቅ ባለርስቶች ሲሆኑ ከሕዝቡ ከፍተኛ ክፍል የሆነው ገበ
ሬ ተበዝባጋርና ተጨቋኝ ጪሰኛ ወይም «የቀን ሠራተኛ» ነው።እፍኝ



የማይሞሉት ባለሃብቶች ሰልጥነውና ተንደላቀው ሲኖሩ ከሰማንያ በመ
ቶ እስከ ዘጠና በመቶ የሚሆነው ሕዝብ በረሃብ፤በድንቁርና፤በበሽታ፤
እንደተጠቃ ይኖራል፤ይሞታል።እዚህ የስንቱን አገር ስም በምሳሌነት
ጠርቶ ይዘለቃል! ከሁሉ የሚመለከተንን የሃገራችንን ሁኔታ ለመጥቀ
ስ ያህል፤በኢትዮጵያ በያንዳንዱ ሰው —የነፍስ ወከፍ— ያመት ገቢ ሃ
ምሳ ዶላር፤ዘጠና አምስት በመቶው ሕዝብ መሃይም፤የትምህርት ዕድ
ሜ ካላቸው ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ አሥር በመቶ፤ለሃያ አምስ
ት ሚሊዮን ሕዝብ ስድስት መቶ ሐኪም ብቻ!! እነዚህ የዩኔስኮ ስታ
ቲስቲኮች ናቸው።በአፍሪካ ውስጥ ኢትዮጵያ የምትቀድመው አገር
ማላዊን ብቻ ነው፤ደግሞም ያሁኑ የሕብረተሰባችን አቋም እንዳለ ከቀ
ጠለ በቅርቡ ማላዊ ቀድሞን የሕዝቦች መደምደሚያ እንደምንሆን ጥ
ርጥር የለውም።በዛሬው ዓለም ከኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ የተበዘበዙ
ና የተጨቆኑ አገሮች በጅ ጣት ይቆጠራሉ።

በተበዝባጋ አገሮች በሥልጣን ላይ የሚገኙት አድሃሪ መ
ደቦች ከሠራተኛውና ከገበሬው የሚዘርፉትን የላብ ፍሬ መልሰው ለገ
በሬውና ለሠራተኛው መጨቆኛ መሣሪያ መግዣ ያውሉታል።የወታደ
ርና የፖሊስ ኃይላቸውን ያዳብሩበታል።ሁሉ በጃቸው፤ሁሉ በደጃቸው
የሕዝቡ ሕይወት በነርሱ ዘንድ ከጋሠሥ ሕይወት የበለጠ ዋጋ የለው
ም።በተበዝባጋ አገሮች ያሉት ወጣቶች የሚታገሉት እንደዚህ ያለ
ውን ኢሰብዓዊ ሕብረተሰብ ለመደምሰስና በቦታው በመብት፤በኩልነ
ት፤በወደፊት እርምጃ ላይ የተመሠረተ ሕብረተሰብ እንዲተካ በማለት
ነው።

———

ዓለም–አቀፉን የተማሪዎችና የወጣቶች ትግል ዓይነተኛ
የሚያደርገው በብሔራዊ ደረጃ ግፍንና ጭቆናን፤አድሃሪ አገዛዝን በ
መቃወም የሚፈጽሙት ተጋድሎ መሆኑን ከዚህ በላይ ተመለከትን።
ነገር ግን በዓለም ሁሉም ነገር ከሌላው ጋር የተያያዘ ነው፤የሕዝቦችን
ትግል ነጣጥሎ በብሔራዊና በኢንተርናሽናላዊ ሕይወቶች መካከል ል
ዩነት አድርጎ የማያወላውል፤የማያከራክር ድንበር ለማሥመር አይቻ

ልም ።

በኢምፔሪያሊስት ፡ በሶሺያሊስትና በተበዝባዥ አገሮች የ
ሚደረጉትን የወጣቶች ተጋድሎዎች የሚያዋህዳቸው ሁለተኛው መ
ልክ እንደሸረሪት ድር በተበዝባዡ ዓለም ላይ የተዘረጋውን የኢምፔሪ
ያሊዝምን የባርነት መረብ ለመበጣጠስ የሚደረገው ውጊያ ነው ።ባሜ
ሪካ የሚመራው የኢምፔሪያሊስት ክበብ በሄደበት ሁሉ ከሕብረተሰቡ
ፍጹም አድሃሪ የሆነውን መደብ ከሥልጣን ላይ ያስቀምጠዋል ፣ተቀም
ጦ አግኝቶትም እንደሆን እንዳይነቃነቅ አንከብክቦ ይይዘዋል ፣በርሱ አ
ማካይነት የራሱን ብዝበዛ ለማከናወን ይመቸዋልና ።በየአህጉሩ በኢም
ፔሪያሊስቶችና በብሔራዊ አድሃሪዎች መካከል የተደረጉትና የሚደረጉ
ት ወታደራዊ፣ባሕላዊ፣ኢኮኖሚካዊ፣የንግድና የዕርዳታ«ስምምነቶች»
ለአድሃሪው መደብ የዕድሜ ርዝማኔ ዋስትናና ለኢምፔሪያሊስቶቹ ብ
ዝበዛ በር መክፈቻ ቁልፎች ናቸው ። የሁለቱም ወገኖች ምኞት የዓለ
ምን ሕዝቦች በጭቆና ይዞ ለዘለዓለም መኖር ነው ።የሕልም እንጀራ !

በኢምፔሪያሊስት አገሮች ሠራተኛውና ወጣቱ ፋሺዝምን
በመቃወም እንደሚታገል ከላይ ተጠቅሷል ። ፋሺዝም የኢምፔሪያሊ
ዝም የመጨረሻ ደረጃ እንደመሆኑ መጠን የላብ–አደሩን ሬቮሉሽን
መድረስ የሚያበስር ታሪካዊ ወቅት ነው ።ከኢምፔሪያሊስት አገሮች የ
ገዛ ሕብረተሰባቸውን የሚያካሂዱትን የቡርዡዋ ሞኖፖሎች በመቃወ
ም ወጣቶቹ የሚያደርጉት ተጋድሎ በዚህ አኳኋን ከመላው ዓለም ፀረ
ኢምፔሪያሊስት ተጋድሎ አንዱ ቅርንጫፍ ሆኖ ይገኛል ።ይህም የላብ
አደሩን የሬቮሉሽን ወቅትና የተጨቆኑትን ሕዝቦች የነፃነት ቀን በርግ
ጥ ያፋጥናል ።

በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት
በኋላ ኢምፔሪያሊዝምን በመቃወም ለብሔራዊ ነፃነት የሚታገሉትን
ሕዝቦች በመደገፍ ይደረግ የነበረው ትግል በርግጠኛ ኢንተርናሽናሊዝ
ም ላይ የተመሠረተና የጠበቀ ነበር ። በነዚህ አገሮች ይመራ የነበረው
የዓለም ተማሪዎች ማህበር — አይ ዩ ኤስ — በዚህ ትግል ውስጥ ያደ
ረገው አስተዋፅኦም ትልቅ ነበር ።ዛሬ የምሥራቅ አውሮፓ ተማሪዎች
ከሁኔታቸው የተነሳ በሚያወላውል አቋም ላይ ይሁኑ እንጂ በተግባር



ዎች ውስጥ የሠራተኛና የገበሬ ልጆች በቁጥር አንድነት ከሃያ አምስት
በመቶ በታች ናቸው(1) ።እንደዚያም ሆኖ ተማሪዎቹ የሚሰለጥኑት ለ
ቡርዡዋዚው የፕሮዳክሽን መኪና እንዲውሉ ነው እንጂ ሕብረተሰብ
ን በተሻለ ሰብዓዊ መንገድ እንዲያደራጁት ወይም ሕይወታቸውን ሰለ
ፊው ሕዝብ አገልግሎት እንዲያበረክቱት አይደለም ። ትምህርቱ በዘ
ዴውም በግቡም አድሃሪ ሆኖ ይገኛል ።ተማሪዎቹ ይህንን ይገነዘቡታል

ቡርዡዋዚው የጥፋት መሣሪያዎችን በብዛት እንደሚሠራና
በፍጥረቱ የሰላም ጠር መሆኑን ሸሽጐ ሊያመልጥ አይችልም ።ስለ ዓ
ለም ሰላም በሚያወራው ወሬና በየዕለቱ « በሕግና በፀጥታ » አመካኝ
ቶ በሚፈጽመው ወንጀል መካከል ትልቅ ቅራኔ አለና ።ተማሪዎች ይህ
ንንም ያውቁታል ።እንግዲህ በብሔራዊ ደረጃ የሚታገሉት ይህንን አ
ድሃሪና ኢሰብዓዊ የሕብረተሰብ አቋም መንቅሎ ለመጣልና ሕዝቡ በ
ፈቃዱ የወደፊት ዕድሉን የሚቀይስበት፣የሕብረተሰብን ሰብዓዊና የተ
ፈጥሮ ሀብት ለጥፋት ሳይሆን ለልማት የሚያውልበት፣እኩልነትና ነፃ
ነት፣አእምሮ የነገሠበት፣ሕብረተሰብ ለመፍጠር እንዲቻል ነው ።

ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ወደ ምስራቅ አውሮፓ አገር
ች ስንዞርም ተማሪዎች በብሔራዊ ደረጃ የሚታገሉት ለነፃነት፣ለዴሞ
ክራሲና ለሶሻሊዝም መሆኑን እናያለን ።በምስራቅ አውሮፓ ሶሺያሊ
ስት ሬቮሉሽን ከተደረገ በኋላ የሠራተኛው መደብ ሥልጣኑን ይዞ ነበ
ር ።ቢሆንም ከታሪክ አስተዳደግ የተነሳ ሥልጣኑን የያዘው የሠራተኛ
መደብ ወዲያውኑ ቡርዡዋዚውን ከነሥረ–መሠረቱ መንቅሎ ሊያጠ
ፋው አልቻለም ።በተለይም በአይዲዮሎጂ፣በሥነጽሁፍ፣በሥነጥበብ፣በ
ባሕልና በጠቅላላውም መኀፈሳዊ አቋም (ሱፐርስትራክቸር) በኩል የ
ሠራተኛው መደብ የማያወላውል ድልን በቡርዡዋዚው ላይ ለማግኘ
ት አልቻለም ነበር ።ከዚህና ከኢምፔሪያሊዝም መስፋፋት የተነሳ በም
ሥራቅ አውሮፓ የሠራተኛው መደብ መሪ የነበረው ፓርቲ ፍጥረቱን
ለውጦ ወደተቃራኒው ተለወጠ ።ከዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ወደ ቢሮክራ
ታዊ ፀረ ነፃነት ፓርቲ፣ከግንባር ቀደምትነት ወደእርምጃ መሰናከል፣የ
ሕዝብ ክፍል ከመሆን ከሕዝብ በላይ ወደመሆን፣ ተለወጠ ።የስንቱን
መቶ ሺህ ጀግኖች ደም አሳልፎ በመስዋዕትነት ለሬቮሉሽኑ በመስጠት

(1) ቁጥር ለተደረገባቸው ሁሉ ተጨማሪ ማብራሪያ በየዕሁ
ፎቹ መጨረሻ ይሰጣል ።

የተገኘው የሠራተኛው መደብ ጥቅምና ነፃነት እየዳበረ በመሄድ ፈን
ታ በቢሮክራታዊው ፓርቲ ጥቅም ተሸፍኖ ቀስ በቀስ እየመነመነ ሄደ
ዛሬ በምስራቅ አውሮፓ የሚታየው የሠራተኛው መደብ ሁኔታ በኢ
ምፔሪያሊስት አገሮች ያለውን ሁኔታ እየመሰለ በመሄድ ለነፃነትና ለ
እርምጃ፤ለአዲስ ዓይነት ሕብረተሰብ የሚደረገውን ጥረት የሚቃወም
ሆኗል፤ማለት፤ፀረ–ሬቮሉሽናዊ ወይም አድሃሪ ሆኗል።

ባንድ በኩል በሥልጣን ላይ ያሉ ቢሮክራታዊ ፓርቲዎች
ለወጣቱ ትውልድ ለመስጠት የሞከሩት የተሳሳተ የሶሻሊዝም ሥዕል
ይህ ሆኖ ስለተገኘ፤በሌላ በኩል ደግሞ የኢምፔሪያሊስት ፕሮፓጋንዳ፤
ጋዜጣው፤በመጽሔቱ፤በሲኒማው፤ወደነዚህ አገሮች ገብቶ የወጣቱን መ
ንፈስ እንዲመርዝ በሩ በሰፊው ስለተከፈተለት፤ላጭር ጊዜ ወጣቱ ት
ውልድ ተታለለ።በሬቮሉሽናዊ ርዕዮተ–ዓለም ፈንታ የኢምፔሪያሊስ
ቶችን «ሥልጣኔ» እንደ መለኪያ ሚዛን ወስዶ በሥልጣን ላይ ያለው
ን ቢሮክራታዊ አቋም ተቃወመ።ነገር ግን ላጭር ጊዜ ብቻ ነው።የቼኮ
ዝሎቫኪያ ወረራ የብዙዎችን ዓይን ከፍቷል፤ዛሬ መከተል ያለባቸውን
መስመር በመፈለግ ላይ ያሉት የምሥራቅ አውሮፓ ተማሪዎች ቀድሞ
ውንም ቢሆን ለማስወገድ የጣሩት ውስጣዊውን ብሔራዊ ቢሮክራቲ
ክ አቋም ነበር።

በኢምፔሪያሊስት አገሮችና በምሥራቅ አውሮፓ ያሉት
ተማሪዎች ትግል ከዚህ በላይ ተጠቅሶአል።በተበዝባዥ አገሮችስ ተ
ማሪዎች በብሔራዊ ደረጃ የሚያደርጉት ትግል ምን ዓይነት ነው?

በተበዝባዥ አገሮች የሕብረተሰብን አቋም ዓይነተኛ የሚ
ያደርገው በሰው ልጆች መካከል ያለው የሃብት ልዩነትና ከርሱም የሚ
ፈልቀው የመብት ልዩነት ነው።በብዙዎች የእስያ፤ያፍሪካና የደቡብ አ
ሜከሪ አገሮች ከአውሮፓ የዛሬ ሦስት መቶ ዓመት የጠፋው ፊውዳላ
ዊ አቋም፤ከኢምፔሪያሊዝም መስፋፋት የተነሳ እንደያገሩ መልኩን
ለውጦ ውጥንቅጥ ይሁን እንጂ፤አሁንም አለ።የሕብረተሰቡ የመጀመ
ሪያና ዋና የፕሮዳክሽን መሣሪያ የሆነውን መሬትን የያዙት እፍኝ የማ
ይሞሉ ታላላቅ ባለርስቶች ሲሆኑ ከሕዝቡ ከፍተኛ ክፍል የሆነው ገበ
ሬ ተበዝባዥና ተጨቋኝ ጪሰኛ ወይም «የቀን ሠራተኛ» ነው።እፍኝ



ንዳይንቀሳቀስ በሚፈጽሙ፥ ወንጀል መካከል ግልጽ የሆነ ቅራኔ አለ(3)
ተማሪዎች ይህንን ቅራኔ ከማስተዋላቸው የተነሳ የሕብረተሰብን አቋም
ጠለቅ አድርገው ይመረምሩና አድሃሪዎች በጉልበት ካልተደመሰሱ የ
ተባለው የሰው ልጅ መብት፤ነፃነት፤የወደፊት እርምጃ በርግጥ ከሥራ
ላይ ሊውል አይችልም የሚል መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ።ይህ ዓይነቱ
የሕሊና መዳበር ወደሬቮሉሽናዊ ተግባር ይመራቸዋል።እንዲታገሉ ከ
ሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው።

ነገር ግን ከዚሁ የሕሊና መዳበር ጋር የተያያዘ ሌላ ምክንያ
ት አለ፤ይኸውም የታሪክ ግስጋሴና የተጨቆኑ የዓለም ሕዝቦች ትግል
ያስከተለው የመንፈስ ንቃት ነው።

የዛሬ ሰባ ዓመት እፍኝ የማይሞሉ የምዕራብ ኮሎኒያሊስቶ
ች ዓለምን ተከፋፍለዋት የሕዝቦች ሁሉ ጌቶች ነበሩ።እስከሁለተኛው
የዓለም ጦርነት ድረስ «በንግሊዝ ኢምፓየር ላይ ፀሐይ አትጠልቅም»
የሚባልበት ዘመን ነበር።እንደምዕራብ ኢምፔሪያሊስቶች በዓለም ሕዝ
ቦች ላይ በፈላጭ–ቆራጭነት የፈነጨ ማንም ኃይል አልነበረም።ዛሬስ?
ታላቁ የኦክቶበር ሬቮሉሽን በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍን
ከከፈተ በኋላ፤ዛሬ በምሥራቅ አውሮፓ ሬቮሉሽኑ ለጊዜው ይዳከር እ
ንጅ፤ሲሶው የሰው ልጅ በሶሻሊዝም ሕብረተሰባዊ አቋም ሥር ይተዳ
ደራል።ከታሪክ ዘመናት ጋር ስናመዛዝነው ሃምሳ ዓመት —ካንድ ሰው
ዕድሜ ያነሰ ጊዜ!— በጣም አጭር ዘመን ነው።ባለፉት ሃያ ዓመታት
ውስጥ የዓለም ሕዝቦች በኮሎኒያሊዝም ላይ አንዳንድ ትላልቅ ድሎች
ን በማግኘት ኢምፔሪያሊዝምን አድክመውታል።ይህ ሁሉ ታሪክ በግስ
ጋሴ የወሰደውን አቅጣጫና ረጅም እርምጃ ያሳያል።

የዛሬውን የታሪክ ምዕራፍ ዓይነተኛ የሚያደርገው የዓለም
ተበዝባዥ ሕዝቦች ለብሄራዊ ነፃነት፤ለዴሞክራሲ፤ለሶሻሊዝምና ለዓለ
ም ሰላም የሚያደርጉት ተጋድሎ ሲሆን በዚህ ውስጥ የግንባር ቀደም
ትነትን ቦታ የያዘው የቪየትናም ሕዝብ ተጋድሎ ነው።የቪየትናም ሕዝ
ብ ምሳሌያዊ ተጋድሎ የተማሪዎችን ብቻ ሳይሆን የዓለም ሕዝቦችን ሬ
ቮሉሽናዊ የመንፈስ ንቃት ከፍ ካለ ደረጃ ላይ አድርሶታል።ኢምፔሪያ
ሊዝም ወደ መቃብሩ የሚጓዝበትና የዓለም ሕዝቦች በድል ጉዳና የሚ

ገሰግሱበት ዘመናችን ለሬቮሉሽን ምቹ መሆኑን ተማሪዎች ተረድተው
ታል።በዚህ ምክንያት መስዋዕትነትን ሳይፈሩ እንዲታገሉ ተገፋፍተዋል

ተማሪዎች እንዲታገሉ የሚገፋፏቸውን ምክንያቶች ባጭሩ
ከዚህ በላይ ተመለከትን።የተማሪዎች ተጋድሎ ሕብረተሰብን ከምን ያደ
ርሰዋል? መስዋዕትነታቸው እንዲሁ በከንቱ ይቀራል ወይስ የሚያተርፈ
ው ነገር አለ?

---

የሕብረተሰብ አቋም ፊውዳላዊም ሆነ ቡርዡዋ ወይም ቢ
ሮክራታዊ–ቢሮክራሲም በመሠረቱ የቡርዡዋ ሕብረተሰብ አቋም ነው
ና–እውነተኛ የሰው ልጅ ነፃነት እንዲኖር ከተፈለገ ሰፊው ሕዝብ የ
ገዢዎችን መደብ በኃይል ደምስሶ ሥልጣኑን በጁ ማግባት አለበት።
አድሃሪዎች በገዛ ፈቃዳቸው ከሥልጣን ሲወርዱ በሰው ልጅ ታሪክ
ታይቶ አይታወቅም፤ወደፊትም ሊሆን የማይችል ነገር ነው።በኃይል መ
ደምሰስ አለባቸው፤ሌላ መንገድ የለም።እውነተኛው የሰው ልጅ ነፃነት፤
እኩልነትና የወደፊት እርምጃ እንዲኖር ከተፈለገ ገበሬውና ሠራተኛ
ው ተደራጅቶ ሬቮሉሽን በማድረግ አዲስ ዓይነት ሕብረተሰብ መፍጠ
ር አለበት።

ነገር ግን ሬቮሉሽን ቀላል ነገር አይደለም።ሬቮሉሽን የሕብ
ረተሰብ ጠቅላላ ሹም–ሽረት ነው(4)።አሮጌውን ለማጥፋት የሚደረገ
ው ጠቅላላ ድብልቅልቅ በውስጡ ያዲሱን ሕብረተሰብ ጥንስስ ይዞ ቢ
ገኝም ሬቮሉሽን ማለት መስዋዕትም ማለት ነው።ቢሆንም ለነፃነት መጋ
ደል፤መብትን መጠየቅ ራሱ አስቀድሞ ነፃ መውጣት መሆኑን እንርሳ
በዚህ መሠረት ሬቮሉሽን ማለት ነፃነትም ማለት ነው።ሰፊው ሕዝብ ተ
ደራጅቶ ከተነሳ ነፃነቱን ከቀሚዎቹ በኃይል ለመንጠቅና አዲስ ሕብረተ
ሰብን ለመፍጠር ችሎቲ አለው።

ሆኖም «ሬቮሉሽንን ለማድረግ ሬቮሉሽናዊ ፓርቲ መኖር አ
ለበት»፤ባገሩና ባካባቢው ዝርዝር ሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሠረተ «ሬ
ቮሉሽናዊ ቲዊሪ መኖር አለበት»።የተማሪዎች ተጋድሎ የቱንም ያህል



ኃይለኛ ቢሆን በፍጥረቱ እነዚህን ሁለት ነገሮች በቀጥታ ለማበርከት አ
ይችልም፡ከሕብረተሰባዊ ሁኔታቸው የተነሳ ተማሪዎች ሰፊውን ሕዝ
ብ በግንባር ቀደምትነት ለመምራትና ወደ ድል ለማድረስ አይችሉም።

የተማሪዎች ተጋድሎ የሰፊውን ሕዝብ ሬቮሉሺናዊ መንፈ
ስ ከፍ እንደሚያደርገው ከላይ መላልሰን ጠቅሰናል።አድራጎታቸው
ሰፊው ሕዝብ በራሱ ኃይል እንዲመከና አንድነቱን አጠንክሮ ከተዋጋ
ሊያሸንፈው የሚችል ማንም ኃይል እንደሌለ እንዲገባው ያደርገዋል፤
ወደድርጅት ይገፋፋዋል።ይህ ትልቅ አስተዋፅዖ ነው።

ነገር ግን የተማሪዎች አስተዋፅዖ በዚህ ብቻ አይወሰንም።
ጥቂቶች በትግል እሳት የተፈተኑ፤የላብአደሩን መደባዊ አይዲኦሎጂና
አቋም የግላቸው ያደረጉ፤ሕይወታቸውን ለሕዝቡ አገልግሎት፤ለሬቮሉ
ሺን ለማዋል ቆርጠው የተነሱ፤እነዚህ ተማሪዎች በግንባር ቀደምትነት
በኋላ መሰለፋቸው አይቀርም።በዚህ አስተያየት የተማሪዎች ትግል እን
ደሬቮሉሽናውያን መመልመያና ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ሊቆጠር ይ
ችላል።

የተማሪዎች ሬቮሉሽናዊ የመንፈስ ንቃት ዙሮ ዙሮ የሚ
መነጨው ከሕዝቦች ዕለታዊ ትግል መሆኑንና ትግላቸው ደግሞ በበኩ
ሉ የሕዝቦችን ሬቮሉሽናዊ መንፈስ ከፍ እንደሚያደርገው ከዚህ በላይ
አይተናል።ሁለቱ እንቅስቃሴዎች ተደጋጋፊና ተጣማሪ፤ያንድ ትግል ቅ
ርንጫፎች እንደመሆናቸው መጠን ዲያሌክቲካዊ አስተዳደግ አላቸው፤
አንደኛው ከፍ ሲል ሁለተኛው ከፍ ይላል፤የሁለቱ መንታ እድገት ሕ
ብረተሰብን በጠቅላላው ወደፊት ያራምዳል።

ነገር ግን ተጋድሎአቸው የበለጠ ውጤትን እንዲሰጥና የሬ
ቮሉሽንን ወቅት እንዲያፋጥን ከፈለጉ ተማሪዎችና ምሁራን ከገበሬው
ና ከሠራተኛው ጋር መዋሃድ አለባቸው።«ተማሪና ምሁር ከገበሬውና ከ
ሠራተኛው ጋር ተዋህዶ፤ከነርሱ ተማር፤መልሰህም አስተምራቸው» የሚ
ለው መሪ ቃል ዛሬ ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ ከሥራ ላይ መዋል አለ
በት።በተለይም ባገራችን ጊዜያዊ ሁኔታ የወጣቶች ከገበሬውና ከሠራተ
ኛው ጋር መዋሀድ ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ከገራችን የሚጠ
ፉበትን ቀንና በነፃነትና በኩልነት ላይ የተመሠረተች አዲስ ሕዝባዊት

ሕዝባዊት ኢትዮጵያ የምትወለድበትን ቀን እንደሚያፋጥን አይጠረጠ
ርም።የሕብረተሰብን ጠቅላላ አቋም፣የዓለም ሕዝቦችንና የዓለም ተማሪ
ዎችን ተጋድሎ፣የሰውን ልጅ ታሪክና ግስጋሴውን፣የሕይወትን ትርጉም
ከጠና በኋላ ሕይወቱን ለሕዝቡ አገልግሎትና ለነፃነት ትግል የሚያው
ል ወጣት ሁሉ በዚህ አድራጎቱ ብቻ አስቀድሞ ራሱ ነፃ የወጣ ሰው
መሆኑን መረዳት ይገባዋል።

## ማብራሪያዎች

(1) እግረ መንገዳችንን፣«ውይይት» በሚባለው የኢ.ት. አስተማሪዎች
መጽሔት ቁጥር ፪፤አቶ መስፍን ወልደ ማርያም ስለ ዩኒቨርሲቲ አገባ
ብና ስለተማሪው የትውልድ መደብ የሚያቀርበውን ስህተተኛ አስተያ
የት ተመልከት።በአቶ መስፍን አስተያየት በምዕራብ አገሮች የዩኒቨር
ሲቲ መግቢያ መመዘኛ (ክራይቴሪያ) የተማሪው መደብ ሳይሆን «ችሎ
ታው» ብቻ ነው!! በምዕራብ ዩኒቨርሲቲዎች ስለተማሪዎች መደብ በሚ
ቀጥሉት ገጾች ስታቲስቲክ ተጠቅሷል ።

(2) ለምሳሌ ከኢምፔሪያሊስት አገሮች የፈረንሣይ አገርን ተማሪዎ
ች ብንወስድ፣8 በመቶ የገበሬ ልጆች፣14 በመቶ የሠራተኛ ልጆች፣22
በመቶ የፔቲ ቡርዦዎ፣56 በመቶ የቡርዦዎ ልጆች ናቸው።በኢምፔሪ
ያሊስት አገሮች በሙሉ ከሞላ ጎደል ይህንኑ የመሰለ አከፋፈል አለ።
ከምሥራቅ አውሮፓ ለምሳሌ በፖላንድ በ1951 ዓ.ም ዩኒቨርሲቲ የተ
ቀበላቸው ተማሪዎች 39 በመቶ የሠራተኛ፣25 በመቶ የገበሬ፣36 በመ
ቶ የቢሮክራሲው ልጆች ሲሆኑ፣በ1961 ዓ.ም ግን – ከሥር ዓመት በ
ኋላ – 28 በመቶ የሠራተኛ፣19 በመቶ የገበሬ፣53 በመቶ የቢሮክራት
ልጆች ነበሩ።የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ወዴት እንደሚገሰግሱ ያሳ
ያል።እነዚህ ቡርድዩና ፓስሮን የሚባሉ የፈረንሣይ ዩኒቨርሲቲ አስተ
ማሪዎች ከጻፉት «Les Iteritiers» (Paris 1966) ከሚባለው መጽሐ
ፍ የተቀዱ ናቸው።ነገር ግን ማንኛውንም የተማሪዎችን መደብ የሚመ
ለከት ስታቲስቲክ ተመልከት ።



## «ከሕዝቡ ጋር ተሰለፍ፣ከሱ ተማር፣አብረኸው ታገል»

ከገብሬ ሂባ

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ለአባሎች በሙሉ «ከሕዝ
ብ ጋር ተሰለፍ፣ከሱ ተማር፣አብረኸው ታገል»የሚለውን መሪ ቃል ደ
ጋግሞ አሰተላልፎአል።

ከሕዝብ ጋር መሰለፍ፣ከሱ መማርና አብሮት መታገል ምን
ማለት ነው?እውቀትን ለማትረፍ ነውን?ወይስ ብሩሕነትን ለማትረፍ
ነው?አባሎች ብሩሕና አዋቂ ምሁራን እንዲሆኑ ነውን?

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ይህን መሪ ቃል ያስተላለፈ
ው የአለምን ሕዝብ ታሪክ ግስጋሴና የኢትዮጵያን ሕዝብ (ማለት የሠ
ራተኛውንና የገበሬውን ) የትግል ደረጃ ጠልቆ በማጥናትና በመመር
መር ነው ።

ዛሬ በዓለም ላይ እንደምናየው ብዙ ሕዝባቸውን እየጨቆ
ኑና እየዘረፉ የሚኖሩ የሕዝብ ጠላት የሆኑ መንግሥታት አሉ ።እነዚ
ህም ሕዝባቸውንና አገራቸውን ለጥቅማቸው ሲሉ አሳልፈው ለባዕድ
አገር የሚሸጡ መንግሥታት በእስያ፣በላቲን አሜሪካና በአፍሪቃ ተስ
ፋፍተው ይገኛሉ ።

በክፍለ ዓለማችን በአፍሪቃ ለምሳሌ፣እንደነአንክራና እንደ
ነታራአሬ ፀረ–አፍሪቃና የኢምፔሪያሊስት ቡችላ የሆኑ፣እነንክሩማንና
እነሞዲቦ ኬይታን በመሰሉ የአገራቸውና የሕዝባቸው ፍቅር በሞላባ
ቸው ብሩህ መሪዎች ቦታ ሲተኩ ባለፉት ዓመታት አይተናል።የነዚህን
ሁኔታዎች መሠረታዊ ምክንያት ለማወቅ በምንፈልግበት ጊዜ ራሳችን
ን የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቅ አለብን፤– እንዴት ነው በጋናና በማ
ሊ እንደዚህ አይነት የኢምፔሪያሊስት አሻንጉሊት መንግሥታት ለማ
ቆም ሲቻል ከብዙ ጊዜያት ጀምሮ ሌት ተቀን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊ
ዝም የቦምብ ናዳ በሚያወርድበት በሰሜን ቪየትናም ኩ–ዴታ ማድረግ
ያልተቻለው ?

በጋናና በማሊ የመንግሥቶቹን ቢሮክራሲ የሚያካሄዱት
ቢሮክራቲክ ካፒታሊስትና የፊውዳል ክፍሎች ንክሩማና ሞዲቦ ከሠራ

አገራችን በኢምፔሪያሊዝም የተረገጠች እንደመሆኗ መ
ጠን ተማሪና ምሁራን በብዛት ትምህርታቸውን የቀሰሙት በምዕራብ ኢ
ምፔሪያሊስቶች በሚካሄዱ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች ነው። በ
ነዚህ ትም. ቤቶች ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት በቡርዡዋ ርዕዮተ– ዓ
ለም—ማለት በካፒታሊስቱ ክፍል የጭቆናና የዘረፋ ርዕዮተ–ዓለም—
የተሞላ ስለሆነ የሚያገኙት ትምህርት በዚሁ ርዕዮተ–ዓለም የረጠበ ነ
ው።ከዚህም የተነሳ ሕዝቡን መናቅ፤የገበሬውንና የሠራተኛውን መደ
ብ ታሪካዊ ድርጊት ዝቅ አድርጐ መመልከት ባህሪያቸው ይሆናል፤ራ
ሳቸውን እንደ ኤሊት (elite)፤እንደ ጠቢብ፤እንደ ተቀቡ መሪዎች፤
እንደ ሊቃውንት አድርጐ መቁጠርን የመሳሰሉ ጠባዮችን ይገበያሉ።
ቀስ በቀስም በመንሸራተት እነዚህ ተማሪና ምሁር ላብ–አደሩን ሕዝቡ
ከሚጨቁነውና ሃገሪቱን ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር እየተዋዋለና እየተባ
በረ ከሚዘርፈው ቢሮክራቲክ–ካፒታሊስት መደብ ውስጥ ይሰምጣሉ።

አሁን ባለንበት ዘመን፤ከዓለም ሕዝብ ትግል ብርታትና ከ
ኢምፔሪያሊስቶች መሸነፍ የተነሳ የቀጥታ ዘረፋ መሣሪያ የነበረው ቅኝ
አገዛዝ ከዓለም ገጽ በሙሉ እየጠፋ በመሄድ ላይ ነው።ቢሆንም ኢም
ፔሪያሊስቶች የዘረፋና የጭቆና ሥራቸውን በአገራችን—እንዲሁም በ
መሰል አገሮች—ለረጅም ጊዜ ለማድራት ስለሚፈልጉ የቀጥታ አገዛ
ዙን መዝረፊያ መሣሪያ የሚተካ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መፍጠር አስፈ
ለጋቸው።የዚህም እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ (neo-colonealism) ቀላል
መሸጋገሪያና ሥልጡን ተጠሪ በነሱ አይዲዎሎጂ የታጠበው የቡርዡዋ
መደብ—ራሱን ያልቻለ መሆኑን እንርሳ—ስለሆነ የዚህ ክፍል መስፋ
ፋት የኢምፔሪያሊስቶች ምኞት ነው።አብሶ እንደ ኢትዮጵያ ዘጠና ከ
መቶ በላይ የሚሆኑ መሃይምናች በሚገኙበት አገር የጥገኛው ቡርዡ
ዋ መደብ መስፋፋት የኢምፔሪያሊስቶች ትልቅ ግብ ነው።

ስለዚህ ነው ኢምፔሪያሊስቶች በተቻላቸው መጠን ስኮላር
ሽፕ በመለገስ፤አስተማሪ በመላክ . . . ወዘተ. ሕዝብ ከሃዲ የሆኑ የሃሳብ
ዲቃሎቻቸውን ለማራባት የሚጥሩት።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ይህን ሁኔታ በደንብ ጠል
ቀው ስለተረዱ ከሃገሪቱ ተማሪዎችና ምሁራን መሃከል የሕዝቡን—ማ



ለት የላብ አደሩን—ወገን የሚደግፈው ክፍል እየጠነከረና እየበዛ ሊሄ
ድ የሚችለው እነዚህ ምሁራንና ተማሪዎች ይህን የተሸከሙትን ብት
ቶ ርዕዮተ–ዓለም አራግፈው ሲጥሉ፤ከሕዝቡ ጋር ሲተሳሰሩና ከሱ ሲ
ማሩ መሆኑን ደጋግመው ገልጸዋል።

ከሕዝቡ ለመማር የሚቻለው በሃገር ውስጥ ያሉት በአካ
ባቢያቸውና በትምህርት ቤታቸው ዙሪያ ካለው ሕዝብ ጋር ሲዋሀዱ፤
በውጭ አገር ያሉት ደግሞ በሬቮሉሽናዊ ድርጅቶች ሥራ ውስጥና በስ
ብሰባቸው ሲሳተፉ፤ሬቮሉሽናዊ ትምህርትንና ሬቮሉሽናዊ ዜናን የሚሰ
ጡ መጽሔቶችን ሲያነቡ፤ባሉበት አገር ከሚገኙ ግንባር ቀደም የሠራ
ተኞች ድርጅቶች ጋር ጥብቅ ግንኙነት ሲያደርጉ ነው።

## ሐ) ከሕዝቡ ጋር አብሮ መታገል፡–

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶቹን ለማጥፋትና የሕይወቱን
አመራር በእጁ ለማግባት በያለበት በመታገል ላይ ነው።ያለማቋረጥ በ
ሚያደርገው ተጋድሎ ጨቋኞቹን ፋታ ነስቷቸዋል።መሠረተ ፍላጐቱም
ይህ አድሃሪዊ መንግሥት የሚወድቅበትን ቀን ማፋጠን መሆኑን አሳይ
ቶናል።ከሕዝቡ ጋር አብሮ ለመታገል የቆረጡ ምሁራንና ተማሪዎች ሕ
ዝቡ በወጠነው ትግል ውስጥ ገብቶ መሳተፍ፤ከጠላቶቹ የሚሰነዘሩትን
የጥቃት ሙከራዎች አብሮ በመከላከል የሕዝቡን ችግር ሁሉ ለማስወገ
ድ መጣር አለባቸው።አሁን ባለንበት ጊዜ ዋናው የህዝቡ ችግር የግን
ባር–ቀደም ድርጅት ጉድለት ስለሆነ፤የሕዝቡን ወገን የመረጠ ምሁር
ሁሉ፤ይህን ችግር ለማስወገድ በርትቶ መሥራት፤በልዩ ልዩ ድርጅቶች
ሥራ ውስጥ በሰፊው መሳተፍ አለበት።

1ኛ) በሕብረሰባችን ውስጥ ያሉት ልዩ ልዩ መደቦች ምን
ም ለዚህ ለወደኋላ ተመልካች መንግሥትና ለበላይ
ጠባቂው ጥላቻ ቢኖራቸው ስለሃገሪቷ የወደፊት አስ
ተዳደር ልዩ ልዩ አስተያየት አላቸው፤ስለዚህ የሁሉም
ጊዜያዊ ግብና ዓላማ ጠላታቸውን ፊውዳላዊውን መ
ንግሥት መደምሰስ ቢሆንም የሚያቋቁሙዋቸው ድ
ርጅቶች የተለያየ አቋም ይኖራቸዋል።

## እንዳንድ ምርጥ ጥቅሶች፡-

"If we have a correct theory but merely prate about it, pigeonhole it and do not put it into practice, then that theory however good, is of no significance."

MAO

"Theory becomes a material force as soon as it has gripped the masses."

MARX

"The people, and the people alone, are the motive force in the making of world history."

"The masses are the real heroes, while we ourselves are often childish and ignorant, and without this understanding it is impossible to acquire even the most rudimentary knowledge."

MAO

"The oppressed peoples and nations must not pin their hopes for liberation on the sensibleness of imperialism and its lackeys. They will only triumph by strengthening their unity and persevering in their struggle.

MAO